ስለ 2015 በጀት ዘመን የMCPS የስራ ማስኬጃ በጀት ግንዛቤ ይኑርዎት

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለሚመጣው የትምህርት ዘመን (2014-2015) የ$2.3 ቢልዮን የስራ ማስኬጃ በጀት ሀሳብ አቅርቧል። በጀቱ ከዚህ አመት በጀት በ4 በመቶ ይበልጣል የስቴት ህግ ከሚጠይቀውም አነስተኛ የገንዘብ ገደብ ልክ ከ2.5 በመቶ በላይ ነው። ይህ በጀት MCPS ለሁሉም ተማሪዎች በአለም ደረጃውን ለጠበቀ ትምህርት መዳረሻ ማቅረብ መቀጠል የሚያስችለው ሲሆን—

- የምዝገባ አድገቱን ያስተዳድራል፣
- የግኝት ክፍተቶችን ለማጥበብ መዋእለ ነዋይ ፈሰስ ያደርጋል፣
- ተማሪዎቻችንን ለወደፊት ያዘጋጃል።

የቦርዱ በጀት ጥያቄ በተወሰኑ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመማርያ ክፍሎች የተማሪ መጠን ለመቀነስ፣ የአማካሪዎችንና የሌሎች የተማሪ ድጋፍ ሰራተኞችን ቁጥር ለመጨመር፣ ለት/ቤቶች ተክኖሎጂ ለማሳደግ፣ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አገልግሎት ለማሻሻል የሚያግዙ ስልታዊ የመዋእለነዋይ ፈሰሶች ያደርጋል። ስለቦርዱ የበጀት ጥያቄ በMCPS Operating Budget (የስራ ማስኬጃ በጀት) ድርጣብያ በመከታተል ግንዛቤ ይኑርዎት።

የMontgomery County ምክር ቤት፣ የMontgomery County Public Schools (MCPS)ን በጀት የሚያካትተውን፣ የ2015 በጀት ዘመን (ከጁላይ 1 2014 እስከ ጁን 30 2015) የስራ ማስኬጃ በጀትን በሚመለከት ህዝባዊ ስብሰባዎች ያካሂዳል። ት/ቤቶቻችን እንዴት ገንዘብ እንደሚመደብላቸው ሃሳብዎን ከካውንቲው መሪዎች ጋር ለመጋራት ይህ አንድ እድል ነው። ስብሰባዎቹ የሚከናወኑት፡-

- ማክሰኞ፣ ኤፕረል 8 በ7 p.m.
- ሮብ፣ ኤፕረል 9 በ1:30 p.m. እና በ7 p.m
- ሀሙስ፣ ኤፕረል 10 በ1:30 p.m. እና በ7 p.m

በነዚህ ስብሰባዎች በአንዱ ቃልዎን ለመስጠት፣ 240-777-7803 ይደውሉ።

ይበልጥ ይማሩ

**የሚቀጥለው/የምትቀጥለው የMCPS የአመቱ መምህር ማን ይሆናል/ትሆናለች?**

ለ2014-2015 የአመቱ መምህር ሽልማት ለመጨረሻው ዙር ውድድር ሶስት የMCPS መምህራን ተሰይመዋል። ሶስቱ መምህራን የMarian Greenblatt Education Fund (የማሪያን ግሪንብላት የትምህርት በጎ አድራጎት) Veteran Teacher Award (ልምድ ያለው መምህር ሽልማት) ተሸላሚዎች ናቸው። ተሸላሚዎቹም፡-

- Kathryn Hageman (ካትሪን ሀግማን)፣ በጌይተርስበርግ የDiamond Elementary School የ5ኛ ክፍል አስተማሪ
- Jane Lindsay (ጄይን ሊንድሴይ)፣ በፑልስቪል የJohn Poole Middle School የስምንተኛ ክፍል የእንግሊዘኛ አስተማሪ
- Aaron Shin (አሮን ሺን)፣ በሮክቪል የParkland Middle School የስምንተኛ ክፍል የዩ.ኤስ. ታሪክ አስተማሪ

The Greenblatt Education Fund በተጨማሪ Deborah Yun (ዴቦራ ዩን)፣ በሲልቨር ስፕሪንግ የአምስተኛ ክፍል አስተማሪን የ2014 Rising Star Teacher of the Year (ያመቱ ኮከብ አስተማሪ) ብሎ በመሰየም ክብርና ሰጥቷል። ይህ ሽልማት የፈጠራ ችሎታቸውና ጉጉታቸው ተማሪዎችን ወደፊት እንዲገፉና ይበልጥ ግኙነት እንዲኖራቸው የሚያበረታቱትን አንደኛ- ወይም ሁለተኛ- የአመቱ መምህር ብሎ ያከብራል።

የአመቱ መምህር የመጨረሻ ዙር እጩዎች በመምህራን ሸንጎ አባላት፣ በትምህርት ቦርድ አባላት፣ በMCPS ሰራተኞች፣ እና የMontgomery County የPTAዎች ምክር ቤት ተጠሪዎች፣ እንዲሁም የግሪንብላት ቤተሰብ አባል ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸዋል።

የMCPS የአመቱ መምህር በኤፕረል 29 በሚከናወነው Champions for Children Awards Celebration (የልጆች ሽልማቶች ሻምፕዮና በአል) ላይ በይፋ ይነገራል። በአሉ የንግድ ስራ ተቋማትና የማህበረሰብ የትምህርት ሻምፕዮኖችንም ያከብራል።

[በተጨማሪ ይማሩ]

**የሙአለህፃናት መተዋወቂያ ፕሮግራም ማርች 31 ይጀምራል**

የ2014 የሙአለህፃናት መተዋወቂያ ፕሮግራም ማርች 31 ይጀመራል። በመተዋወቂያው ወቅት፣ ወላጆችና ተማሪዎች ከት/ቤቱ ርእሰመምህር፣ የሙአለህፃናት መምህራንና ከሌሎች የስራ ባልደረቦች ጋር ይገናኛሉ።

ፕሮግራሞቹ—በያንዳንዱ ኤሌሜንታሪ ት/ቤት ከማርች 31 እስከ ሜይ 30 ለመከናወን የተተለሙት—እድሚያቸው እስከ ሴፕቴምበር 1 2014 አምስት ለሚሞላ ልጆችና ለወላጆቻቸው ነው። ወላጆች ወደ አካባቢያቸው ት/ቤት በመደወል ለዚያ ት/ቤት ለተወሰነ ቀን(ኖች) ለመመዝገብ ቀጠሮ መያዝ አለባቸው። የትኛው ኤሌሜንታሪ ት/ቤት አካባቢያቸውን በተሻለ ሊያገለግል እንደሚችል እርግጠኛ ያልሆኑ ወላጆች በ240-314-4700 ለBoundaries Office መደወል ወይም የMCPSን ድርጣብያ [School Assignment Locator] (የት/ቤት ምደባ ጠቋሚ) ማየት አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ፣ በ301-230-0691 ለDivision of Early Childhood Programs and Services (ለህፃናት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ክፍል) ይደውሉ።

[የሙአለህፃናት መረጃዎች]

**ጊዜዎን ያበርክቱ፤ ከፍተኛ ልዩነት ይፍጠሩ**

የስፕሪንግ እረፍት ጊዜ ለተማሪዎች በአገልግሎት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ እና Student Service Learning (የተማሪ አገልግሎት ትምህርት) (SSL) ሰአቶች ለማግኘት የሚያስችላቸው ታላቅ አመች ጊዜ ነው። ተማሪዎች በተለያዩ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ ይችላሉ፦— በሱፕ ኪችን (ለድሆች በነፃ ምግብ የሚሰጥበት) ለመስራት፣ ያካባቢ መናፈሻ ቦታ ማፅዳት፣ ወይም ለችሮታ ልብስ ወይም ምግብ ማሰባሰብ። ሁሉም የMCPS ተማሪዎች ከ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለመመረቅ 75 የSSL ሰአቶች ያስፈልጓቸዋል። [ለSSL ሰአቶች የፀደቁ] ድርጅቶችንና እድሎችን ፈልጋችሁ አረጋግጡ። በተጨማሪ፣ በሁለተኛው ሴሜስተር የተከናወኑ ሁሉም የአገልግሎት ሰአቶች ለት/ቤቱ SSL አስተባባሪ ከአርብ፣ ጁን 6 በፊት ገቢ መሆን አለባቸው።

በኤፕሪል ወር የመጀመርያው አርብ ላይ የSSL ምረቃ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የSuperintendent Student Service Learning Award (የበላይ ተቆጣጣሪ የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት) ሽልማት ለመቀበል ብቁ መሆናቸውን ያውቃሉ ወይ? 260 ወይም ከዚያ በላይ የSSL ሰአቶች ያላቸው የ2ኛ ደርጃ ት/ቤት የመጨረሻ አመት ተማሪዎች Certificate of Meritorious Service (ሽልማት የሚገባው አገልግሎት የምስክር ወረቀት) እንደሚያገኙስ? ስለ ሁለቱም ሽልማቶች ሰነዶች ከአርብ፣ ኤፕረል 4 በፊት ት/ቤት ለተመደበው የSSL አስተባባሪ መድረስ አለባቸው።

[የተማሪ አገልግሎት ትምህርት]

**የተማሪ ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም (Student Emerging Leaders Program) የጊዜ ገደብ ኤፕረል 11 ነው።**

የተማሪ ታዳጊ መሪዎች ፕሮግራም (Student Emerging Leaders Program)፣ የMCPS እና የMontgomery County Business Roundtable for Education (የንግድ ስራ የጠረጴዛ ክብ ለትምህርት)(MCBRE) የተተለመው ተማሪዎችን በብሄራዊ፣ ስቴት እና ያካባቢ አስተዳደር ግዴታ እንዲሰማቸው በማበረታታት የጥቁርና ሂስፓኒክ መጪው ትውልድ መሪዎች እንዲሆኑ ፍላጎት ለማስፈን ነው። ፕሮግራሙ ተማሪዎችን በምክክር ዝምድና፣ ጓድ-ለ-ጓድ (peer-to-peer) ስብሰባዎች እና የተማሪ ሙግት ያሳትፋል።

ያሁኑ የ9ኛ ክፍል (ታዳጊ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች) ስለ ፕሮግራሙ በተጨማሪ ለማንበብ እና [ለ2014-2015 አመት እዚህ ማመልከት] ይችላሉ።

የማመልከቻ የጊዜ ገደብ አርብ፣ ኤፕረል 11 ነው።

**የከፍተኛ ተሰጥኦ ማእከል ውሳኔዎችን ለመቀበል ወይም ይግባኝ ለማለት የጊዜው ገደብ ኤፕረል 4 ነው**

የኤሌሜንታሪ ማእከል ፕሮግራሞች ለከፍተኛ ተሰጥኦ ላላቸው ለ4ኛና ለ5ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚያበለፅግ፣ የሚያፋጥንና የMCPS ስርአተ ትምህርት የሚያስፋፋ የትምህርት አሰጣጥ ያቀርባል። ለነዚህ ፕሮግራሞች ማመልከቻ ላቀረቡ ተማሪዎች ፈተና በጃኑዋሪ ወር ተሰጥቷል የውጤት ማስታወቂያ ደብዳቤዎችም በማርች አጋማሽ በፖስታ ይላካሉ።

ለፕሮግራሙ ግብዣ ለመቀበል ወይም Level I ይግባኝ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አርብ፣ ኤፕረል 4 ነው። የይግባኝ ማመልከቻዎችን በ301-649-8155 ፋክስ ማድረግ ይቻላል ወይም በፖስታ ወደዚህ አድራሻ መላክ ይቻላል፡- Division of Consortia Choice, Spring Mill Field Office, 11721 Kemp Mill Road, Silver Spring, MD 20902። የይግባኝ ውሳኔዎች በሜይ ወር መጀመርያ ላይ ይሰጣሉ።

[የከፍተኛ ተሰጥኦ ማእከሎች]()

**የMontgomery County መዝናኛ ስራ በአል (Recreation Job Fair) ማርች 28 ይካፈሉ**

የሰመር ስራ የሚፈልጉ ተማሪዎች ወደ Montgomery County የመዝናኛ መምርያ የሰመር ካምፕ ሰራተኞችና አመቱን በሞላ ጊዜያዊ ሰራተኞች በአል አርብ፣ ማርች 28 ከ11 a.m. እስከ 3 p.m.፣ Bauer Drive Community Recreation Center, 14625 Bauer Dr. in Rockville ብቅ ማለት ይችላሉ።

በየአመቱ፣ የመዝናኛ መምርያ የካምፕ አማካሪዎች፣ የመዋኛ ረዳቶች እና የህክምና መዝናኛ ረዳቶችን የሚያካትት ቦታዎች ለመሙላት ከ300 በላይ የሰመር ካምፕና ጊዜያዊ ሰራተኞችን ይቀጥራል። ከመዋኛ/ውሀ፣ የማህበረሰብ ማእከሎች፣ የሰመር ፕሮግራሞች፣ የወጣቶች ፕሮግራሞች እና ከህክምና መዝናኛ ተወካዮች የከፊል ጊዜ ጊዜያዊ ስራዎችን ለመወያየት እና ቦታው ላይ ቅድመ-ማጣርያ ቃለመጠይቆች ለማከናወን ይገኛሉ።

የስራ በአሉ ነፃ ነው ኢላማውም ከ16 አመት በለይ ለሆኑ ወጣቶች፣ የኮሌጅ ተማሪዎችና መምህራን ነው። አስቀድሞ መመዝገብ አያስፈልግም።

ለተጨማሪ መረጃ፣ 240-777-6810 ደውሉ።